# እንደገና አሁንም እንደገና ለአሣር - እሥር

## ከስዊዘርላንድ የአንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ድጋፍ አደራጅ ጊዚያዊ ኮሚቴ

## <u>የክብርት ዳኛ ወ/ሪት ብርቱካን ሚደቅሳን ህገ ወጥ እስር አስመልክቶ የተሰጠ የአቋም መግለጫ</u>

ልዩ ጣዕምና ለዛ፣ ውብ ቃናው ቅኝት የነበረው የቅንጅት መንፈስ እንደገና ነፍስ ዘርቶ፣ ነፍስ ሆኖ ነፍስን ይታደግ ዘንድ አንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ በአዲስ የቅንጅት የአካልና የመንፈስ ወራሽነት የቆመለትን ራዕይ ዕውን ለማድረግ ታጥቆ የተነሳና ለድል የሚያበቃን ቀጥተኛ መንገድ ነው።

አንድነት የአንድ ፖለቲካ ድርጅት ፓርቲ መርህ የሚገዛባቸውን ሰነዶች በማዘጋጀት ትልቁን የፓርቲውን አካል መሥራች ጉባኤ በተሳካ ሁኔታ ማካሄዱ ይታወቃል። መሥራች ጉባኤውም በረቂቅነት የተዘጋጁትን ሰነዶች በማፅደቅና ከፍተኛ መሪ አካላትን በመምረጥ ለትውልዱ የመጀመሪያ ሴት መሪ የሆኑትን ክብርት ዳኛ ብርቱካን ሚደቅሳን ሊቀ መንበር አድርጎ መምረጡ ይታወሳል።

ከዚህም በተጨማሪ ጉባኤው ከሀገር ውስጥ ምሥረታ ማግሥት ጀምሮ ቀጣይ ተግባራትን በመከወን የራሱን ውስጥ በማዕከል በማደራጀት፣ የማዕከልና የበታች አካላትን የአንድነት ፓርቲ ደንብና ሕግ መሠረት በማድረግ ከማጠናከሩም በላይ በውጭ ሀገርም ደጋፊ አካላትን በማደራጀት ሰላማዊና ለሕግ መከበር የሚደረገውን ትግል አትራፊ የሚያደርጉ ተግባራትን ከውኗል። ይህን ጉልበት ያለውን እንቅስቃሴውን በአካል በቦታው በመገኘት ስለ ዓላማውና ተግባሩ መግለጫ በመስጠት የፓርቲውን ሠነዶች በማስተዋወቅ ረገድ መጠነ ሰፊ ተግባራትን በአጭር ጊዜ ከውኗል።

በአውሮፓም ፍሬያማ ጅምሮች ከሚገኙባቸው አካባቢዎች የስዊዘርላንድ የአንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ድጋፍ ድርጅት አደራጅ ጊዜያዊ ኮሚቴ አንዱ ነው። እንደሚታወቀው በስዊዘርላንድ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን የአንድነት ፓርቲ መርሆችን ተግባራዊ ለማድረግ በአመራሩ በኩል በውጭ ሀገርም የሚያደርጉትን እንቅስቃሴ መደግፍ አለብን ብለው በፈቃዳቸው ተነሳስተው ገንዘባቸውን፣ ጉልበታቸውንና ጊዜያቸውን በማስተባበር ግብረ ኃይል አደራጅተው ጽናት አየራቸው፣ ትግዕሥት መርህቸው፣ ቁርጠኝነት መንገዳቸው እና ትህትና አልባሳታቸው ያደረጉትን ክብርት ዳኛ ብርቱካን ሚደቅሳን በጀኔቫ ሕዳር 14 ቀን 2001 ዓ.ም. / November 23፣ 2008 / በመጋበዝ: እንዲሁም ብርቱ የትግል ፍላጎት የሚታይባቸውን ለትውልዱ መምህር የሆኑትን አቶ አክሉ ግርግሬን ጨምሮ በረቂቅ ስልት እግር ከወርች የታሰረውን የስዊዘርላንድ ሕዝባዊ የነፃነትና የዲሞክራሲ ትግል እግዚአብሔር ይፍታህ በማሰኘት <u>ፈውስ አዳኝ ፍቱን መድኀኒት ሆኗል</u>። የስዊዘርላንድ የጄኔቩ የአንድነት ስብሰባ

1ኛ/ እንክርዳድ ፣ ግርድና ድቃቂ ከስንዴ የተለየበት፣

2ኛ/ የአንድነት ከፍተኛ መሪ አካላት በተለይም የአንስቷ ወጣት ዳኛ ወ/ሪት ብርቱካን ሚደቅሳን የመምራት ስናዊ - ብቃት በውል ያመሳጠረ፣

3ኛ/ “ፍቅር በዓይን ይገባል“ እንዲሉ የመሪና የተመሪ የሀሳብ አንድዮሽን ድልድይ በውል የዘረጋና በተግባር ቃል አዋውሎ ወደ ተግባር ያሸጋገረ፣

4ኛ/ የሴቶችን የብልህነት፣ የሀገር ሀሳቢነት፣ የተቆርቋሪነት እና የእናትነት ውበት በውል ያሰነበበ፣

5ኛ/ ሀገር ውስጥ ለሚካሄደው የሕግ የበላይነት መከበር ትግል ባለቤት የማግኘትን አስፈላጊነት በሚመለከትም ሰላማዊ ትግል እንደ አማራጭ መያዝ ያለበት ስለመሆኑ ያስገነዘበና ያስረገጠ፣

6ኛ/ አጋጣሚውን በመጠቀም በስዊዘርላንድ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች፣ እንዲሁም መቀመጫቸው ስዊዘርላንድ በሆኑ አለም አቀፍ ድርጅቶች ዘንድ ለዲሞክራሲና ለፍትህ የሚደረገውን ሕዝባዊ ትግል አጋዥ ኃይልን በማስገኘት ረገድ የጠቀመና ያተረፈም ነበር።

ከዚህም በላይ የእናታችን የድረሱልኝ የደም እንባ ብሔራዊ ጥሪ የጎረበጣቸው፣ የመረራቸውና የጠዘጠዛቸውን ኢትዮጵያዉያንን በሀሳብም አገናኝቶ አካሉን በመፍጠር ረገድም የተጋ ተግባር በተጨባጭ ለመከወን ያስቻለ ባለ ብዙ ዘርፍ ሕዝበ - ጠቀም ተግባራትን ለውጤት ያበቃ ስብሰባ ነበር።

ይህም በመሆኑ በተገኘው ህሊናዊ ድልድይ መሠረትነት በስዊዘርላንድ የአንድነት የድጋፍ አደራጅ ጊዚያዊ ኮሚቴ ቅድመ መሰናዶውን ያጠናቀቀ በመሆኑ በቅርብ ቀን መሥራች ጉባኤውን አካሂዶ አካሉን በመፍጠር ዘመኑ ከትውልዱ የጠየቀውን ተግባር ለማድረግ ተዘጋጅቷል።

በመሆኑም እጅግ የምናከብራቸው፣ የምንወዳቸው፣ የምንሳሳላቸውና አይተንም ያልጠገብናቸው መሪያችን ክብርት ዳኛ ወ/ሪት ብርቱካን ሚደቅሳ የከወኗቸው ዘመን የማይሽረው የተጋድሎ ታሪክ፣ **ለእኛ የትግል ዓርማችን ነው** ! **ምንግዜም ይመራናል** ! **ኃይልና ጉልበት ሰጥቶን የበለጠ ያጠናክረናል!!!** በተጨማሪም ሀገር ውስጥ ከሚገኘው አካላችን እንዲሁም አባላት፣ በውጭ ከሚገኙ አቻ ደጋፊ አካላት ወይም ጥንስስ አስኳል አካላት ጋር ያለንን የትግል አጋርነት በቁርጠኝነት እየገለፅን :-

ሀ = የመከራ መሬት የሆነችው የእናት ሀገራችን ብሩህ ተስፋ የሆኑት የእህታችን፣ የመሪያችን የክብርት ዳኛ ወ/ሪት ብርቱካን ሚደቅሳ ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ እንደገና አሁንም፤ እንደገና አሁንም እንደገና ለአሣርና ለእሥር መዳረግ፣ እንዲሁም የሰብዓዊ መብት ተሟጋችና የአንድነት ፓርቲ ምክር ቤት አባል የሆኑት ክቡር ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያም መደብደብ ለህሊናችን ልብ ያመረቀዘ ቁስል በመሆኑ ለሕግ የበላይነት መከበር ትግል አስፈላጊውን መስዋዕትነት ለመክፈል በቁርጠኝነት ቃል እንገባለን።

ለ= ባለመታደል ባለማርዳ፣ ባለወርቅ ተክሊል ታሪክ ያላት ሀገራችን ልጆች በእስር፣ በሞት፣ በስደት፣ በበሽታ፣ በርሀብ፣ በአፈና... የመንገላታትን ሰቆቃ በውል በመገንዘብ በስዊዘርላንድ የሚገኙ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እንዲሁም አለም አቀፍ ድርጅቶች የአንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ ሊቀመንበር ክብርት ዳኛ ወ/ሪት ብርቱካን ሚደቅሳ ካለምንም ቅድመ ሁኔታ እንዲፈቱና በኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት ይሰፍን ዘንድ ከጎናችን በመሆን በአምባገነኑ አገዛዝ ላይ ያላቸውን ተፅዕኖ ሁሉ እንዲያደርጉ በታላቅ ኢትዮጵያዊ አክብሮትና ትህትና ጥሪያችንን እናቀርባለን።

ነፃነት ለክብርት መሪያችን ዳኛ ወ/ሪት ብርቱካን ! ! !
ለሕግ የበላይነት ትግል ድል አንድነት ቀጥተኛ መንገዳችን ነው ! ! !
ለኢትዮጵያ ትንሣኤ ፍቅርንና ቅንነትን መርሀችን እናድርግ ! ! !

December 31, 2008